# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ

ወዛደር፣ ገበሬ፣ ነጋዴ፣ ወታደር፣ ምሁር)
መብትና ጥቅም
**የሚታገል ጋዜጣ**

ቁጥር 58 ቀን 21/10/1969

## ዘመቻውና አብዮቱ

ባለፈው ቅዳሜ፣ ሰኔ 18 ቀን 1969፣ በአዲስ አበባ ከተማ የተከናወነው የመደበኛ መለዮለባሹና የህዝባዊ ሰራዊቱ ሰልፍ፣ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ፈጽሞ ታይቶ የማይታወቅ አይነት፣ ወደር የሌለው ሰልፍ እንደነበር ተመልካች ሁሉ ተገንዝቦታል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት በጣም አጭር በሆነ ጊዜ ውስጥ ይህንን ህዝባዊ ጦር ለመሰብሰብ፣ ለማሰልጠንና ለማስታጠቅ በመቻሉ የሃገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተመልካቾችን ሁሉ ሳያስደንቅ እንዳልቀረ ለመገመት ይቻላል፡፡ ይህ ሰራዊት በመደብ ምናጩ፣ በወታደራዊ ትምህርቱ፣ በትጥቁ፣ በብዛቱና እንደዚሁ ከሰፊው ህዝብ በተደረገለትና በሚደረግለትም ድጋፍ በርግጥ ለአብዮታዊት ኢትዮጵያ አንድ ትልቅ ሃይል ለመሆን የሚችል ሰራዊት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

መደበኛ መለዮለባሹና ህዝባዊ ሰራዊት በዚሁ ቀን የተቀበሉት ቃለመሃላ እጅግ በጣም ከባድ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡ ከቃለመሃላው ሰባት ነጥቦች የመጀመሪያው ይህ ሰራዊት የኢትዮጵያን ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተግባር ለመተርጎም መታገል እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ሁለተኛው፣ የአገርን ክብርና ነፃነት፣ የጭቁን ህዝቦችዋን መብት፣ የአብዮቱን ድሎች ለመጠበቅና አዲስ ህብረተሰብን ለመገንባት በሚደረገው ትግል ሰራዊቱ እንደሚሳተፍ ይናገራል፡፡ አምስተኛው ነጥብ አብዮታዊ መለዮለባሹና ህዝባዊ ሰራዊቱ የታጠቀ የወዛደሩና የአርሶአደሩ ክንድ እንደሆኑ ይገለጽና፣ የመጨረሻው ነጥብም መለዮለባሹና ህዝባዊ ሰራዊት የሀገሪትዋን ነፃነት፣ የግዛት አንድነትዋንና የጭቁን ህዝቦችዋን ሰላምና ፀጥታ ለመጠበቅ ቃል እንደገቡ ያስታውቃል፡፡

እነዚህ የቃለመሃላው ነጥቦች እጅግ በጣም ከባድ ናቸው ያልንበት ምክንያት፣ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ዲምክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም በተግባር ለመተርጎም ቃል የገባ ሰራዊት ከሁሉ አስቀድሞ የፕሮግራሙን ይዘት በሚገባ የማዋሃድ ሃላፊነት እንዳለበት ግል ስለሆነ ነው፡፡ የአገርን በብርና ነፃነት፣ የኢትዮጵያን ጭቁን ህዝቦች መብትና የአብዮቱን ድሎች ለመጠበቅ ቃል የሚገባ ሰራዊታም፣ የአብዮታዊት እናት አገርን፣ የብሄራዊ ነፃነትን፣ የጭቁኔ ህዝቦችን መብትና የአዲስ ህብረተሰብን ትርጓሜዎች በሚገባ የመረዳትና ለሌላም የማስረዳት ሃላፊነት አለበት፡፡ እንደዚሁም የወዛደሩና የአርሶአደሩ ክንድ መሆን ማለት በማንኛውም ጊዜና ቦታ፣ በጦርነትም ሆነ በሰላም ወቅት፣ ለነዚህ መደቦች ጥቅምና ደህንነት መቆምንና መስዋትን እንደሚጠይቅ እያንዳንዱ የሰራዊቱ አባል ማወቅ ይኖርበታል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም፣ መደበኛ መለዮለባሹና ህዝባዊ ሰራዊቱ የተቀበሉትን ቃል ኪዳን ከስራ ላይ በሚገባ ለማዋል እንዲችሉ በአብዮታዊ አስተሳሰብ በመታነጽ የከፍተኛ ንቃተህሊና ባለቤት መሆን እንዳለባቸው ከቃለመሃላው ለመረዳት ይቻላል፡፡

ማንም በቀላሉ ሊገምተው እንደሚችል ሁሉ፣ በታጠቅ ሜዳ የሰለጠነውና ቅዳሜ ያንን ታላቅ ሰልፍ ያሳየው ህዝባዊ ሰራዊት እነዚህን የግድ የሚያስፈልጉትን እውቀቶችና እምነቶች በዚህ ባጭር ጊዜ ውስጥ እግኝቶአቸዋል ለማለት አይቻልም። ይሁንናም፣ ይህ ሰራዊት አሁን ባለው ወታደራዊ ትምህርቱ፣ ባለው ትጥቁ፣ የውጊያ ፍላጎቱና የማስማትን አነስተኛ የፖለቲካ ትምህርት ትምህርት ይዞ እንደሚዘምት ይገመታል። አብዩታውያን እንደሚያምኑበት ሁሉ፣ የኢምፔሪያዝምን ሃይሎች ተዋግቶ ለማሸነፍ የመሳሪያ ብዛትና ጥራት፣ ወይንም በባህላዊ ጀግንነት መዋጋት፣ ወይንም የሰራዊቱን ቁጥር ማበዛት ብቻቸውን የድል ዋስትና አይሆኑም። ከሁሉ አስቀድሞ ለመተማመን የሚቻለው በተዋጊው አብዮታዊ ንቃተህሊናና በአብዩታዊ አመራር ላይ መሆኑን የብዙ አብዮታዊ ጦርነቶች ታሪኮች ያስረዳሉ።

መኢሶን አብዮታዊ አመራርን ለዘማቹ ሰራዊት በሚጠይቅበት ጊዜ ይህንን ጥያቄ ጥቂት ግለሰቦችን በሰራዊቱ አመራር ውስጥ እንደማስቀመጥ አድርጎ አይመለከተውም። አብዮታዊ አመራር ማለት ባጠቃላይ የዘመቻን ጉዳዮች፣ ወታደራዊ ጉዳዮችን፣ ከኢትዮጵያ አብዮት መሰረታዊ ጥያቄዎች ጋር ፣ ስለሆነም ለማንኛውም ድርጊት መነሻውንና መድረሻውን የሚያደርግ አመራር ማለት ነው። ይህም፣ ሰራዊቱን በሚመለከተው በኩል፣ በተግባር ሲተረጎም፣ ከላይ እስከታች በርእዮተአለም፣ በአስተሳሰብና በአሰራር ዘዴ፣ በአብዮታዊ ዲሲፕሊን የተሳሰሩ አያሌ ሺህ የፖለቲካ አንቂዎችን ከሰራዊቱ ጋር ማዋሃድና ከተራው ተዋጊ ጋር በጥብቅ እንዲተሳሰሩ ማድረግን ይጠይቃል። ምናልባት የዚህ አይነቶቹን አንቂዎች ለማግኘትም ለማስልጠንም ጊዜ አይገኝም ሊባል ይችላል። ነገር ግን ዘመቻው ከፍተኛ ውጤቶችን እንዲያስገኝ ከተፈለገ፣ ይህ ሰራዊት ቃለመሃላውን በትክክል ከስራ ላይ እንዲያውለውና ተዋግቶ የማሸነፍ እድሉ በጣም ከፍ ያለ እንዲሆን ለማድረግ ከተፈለገ፣ በዚህ ስራ ላይ ለመረባረብ ይቻላል የሚል ግምት አለን።

የዚህ አይነቶቹ አንቂዎች በህዝባዊ ሰራዊቱ ውስጥ ያሉትን ብሄረሰቦች ቋንቋዎች የሚያውቁና በነዚህም ቋንቋዎች የፖለቲካ ትምህርትን ለመስጠት የሚችሉ ከመሆናቸውም በላይ፣ እነርሱም እራሳቸው የኢትዮጵያንና የአለምን ሁኔታዎች በማያቋርጥም መንገድ በመከታተል እውቀታቸውን የሚያዳብሩበት ዘዴ መፈጠር ይኖርበታል። ሊፈጠርም ይችላል። በተረፈም፣ ህዝባዊ ሰራዊቱ በውጊያዎች መካከል የጥቂት ጊዜያትን እረፍቶች ማግኘቱ ስለማይቀር፣ ይህንንም ለከፍተኛ ወታደራዊና የንቃተህሊና ትምህርት የሚመያውልበት ዘዴ ቢፈጠር ይጠቅማል እንላለን።

አብዮታዊ አመራር ሲባል ይህ ብቻም አይደለም። አብዮታዊ አመራር፣ በተለይ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ሁኔታ፣ የማርክሲዝም ሌኒንዝምን ሚሊታሪ ሳይንስ፣ ዲያሌክቲካዊ የውጊያ ስልትን፣ በአዝማችና በዘማች፣ በመኮንንና በተራ ወታደር፣ በአዛዥና በታዛዥ መካከል የሚኖሩትን ግንኙነቶች፣ በጠቅላላውም ያቀርረብና ያሰራር ዘዴን ሁሉ ይመለከታል። በርግጥ እነዚህን ነገሮች ሁሉ ለማቃናትና ለማሟላት ጊዜን ይጠይቃል። ቢሆንም፣ ባንድ በኩል የነዚህ ነገሮች መሟላት የድሉን ወቅት የሚያዘገይ

ሳይሆን እንዲያውም የሚያፋጥነው መሆኑንና፣ በሌላ በኩል ደግሞ የነገሮቹን አስፈላጊነት በሙሉ ልብ ተቀብሎ ይህ ሰራዊት በተቻለ መጠን፣ በማያቋርጥ አኳኋን፣ እየተዋጋ እንዲማርም ለማድረግ መጣር የግድ ያስፈልጋል ብለን እናምናለን።

የኤርትራን ችግር በተለይ በሚመለከተው በኩል፣ የተባለው አብዮታዊ አመራር አስፈላጊነት ሊታለፍ የማይችል ግዴታ ነው። በዚያ መስክ የሚሰማራው ሰራዊት በድርጊቶቹ፣ በሚፈጥራቸው ግንኙነቶች፣ ባቀራረቡ፣ የኤርትራን ሰፊ ህዝብ እምነት ለማትረፍ የሚችል፣ ለሰፊው ህዝብ ደህንነት የሚንከባከብ እንጂ ወዳጅንና ጠላትን ሳይለይ የማይመታ፣ ቢቻልም ሰፊውን ህዝብ የሚያነቃና የሚያደራጅ፣ በዚህ ህዝብ ሊታቀፍ የሚችል ሰራዊት መሆን ይኖርበታል። የዚህን አይነት ሁኔታ ለመፍጠር የሚችል ሰራዊት ተገንጣይ ቡድኖቹን ብቻውን ሳይሆን ህዝቡንም አሰልፎ ስለሚወጋ በርግጥ ድልን ይቀዳጃል። ደግሞም፣ እንኳንስ ተገንጣይ ቡድኖቹ ቀርተው የውጭ ወራሪዎችም በብዙ መቶ ሺህ ተሰልፈው ቢመጡም፣ የዚህ አይነቱ ሰራዊትና ህዝብ ምንጊዜም ቢሆን አሸናፊ ይሆናል። እንደዚህ ካልሆነ ግን፣ የአረብ አድሃሪ ሃይሎችን በፖለቲካ ካልበለጥናቸው፣ በኤርትራ ያሉ አድሃሪ ቢሮክራቶችና ሌሎችም አድሃሪዎች እንደሚመኙት፣ ሰራዊቱ ከሰፊው ህዝብ ጋር ከተጋጨ፣ አብዮታችን እንደሚቀለበስና አንድነታችንም እንደሚናጋ ምንም ጥርጥር የለውም።

በመጨረሻም፣ አብዮታዊ አመራር ማለት በጠላት ሰፈር ያሉትን ቅራኔዎች በሚገባ ተረድቶ የሚጠቀምባቸው፣ ወደአብዮቱ ለመምጣት የሚችሉትን ሃይሎች የሚሰበስብ፣ እስከመጨረሻው ሊተናነቁን የሚፈልጉትን አድሃሪ ሃይሎች የሚበታትንና ነጥሎ የሚመታ፣ ያገር ውስጥንና ያለም አቀፍን ሁኔታዎች እየተከታተለ ለየወቅቱ የሚያገለግሉ የትግል ታክቲኮችን የሚያወጣ አመራር ማለት ነው።

መኢሶን የአብዮታዊ አመራርን ጥያቄ የሚያነሳው እነዚህን ሁሉ የትግሉን መስኮች በማመዛዘንና ዘመቻው እስከተቻለ ድረስ ለኢትዮጵያ አብዮት ከሁሉ ከፍተኛ የሆኑ ውጤቶችን እንዲያስገኝ ለማድረግ ባለው ጉጉት እንጂ፣ የድርጅታችን ተቃዋሚ አሉባልተኞች ለሚያስወሩት ለማንኛውም ሌላ ምክንያት እንዳይደለ አንባቢዎቻችን ሁሉ እንዲያውቁት በዚህ አጋጣሚ ልንጠይቅ እንወዳለን። የመኢሶን ምኞት ከግማሽ ክፍለዘመን በላይ በላይ ተዋርደው፣ ተረግጠውና በኢሰብአዊ ፊውዶ ፋሺስት ስርዓት እጅ እግራቸውን ተጠፍረው የኖሩት የኢትዮጵያ ጭቁን ህዝቦች በአብዮታቸውና በአንድነታቸው ጠላቶች ላይ በተቻለ ፍጥነት ድል እንዲያገኙና አዲስ ህብረተሰብን ለመገንባት እንዲችሉ የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረግ ብቻ ነው።

ድርጅታችን በየጊዜው በወጣቸው ጽሁፎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ትግል ረጅምና መራራ እንደሚሆን ደጋግሞ ገልጾአል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም፣ ፊውዳሊዝምን፣ ኢምፔሪያሊዝምንና ቢሮክራሲያዊ ካፒታሊዝምን ጨርሶ ለመደምሰስና ህዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑሊክን ለመገንባት የሚያስችሉን ሶስት መሳሪያዎች የወዛደር ፓርቲና በዚህ ፓርቲ የሚመሩ ህዝባዊ አብዮታዊ

ግንባርና ህዝባዊ አብዮታዊ ጦር መሆናቸውን በግልጽ አስፍሮአል። እነዚህን ሶስት ፍቱን የአብዮት መሳሪያዎች ለመፍጠርና በነርሱም አማካይነት ሰፊውን የኢትዮጵያን ህዝብ ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሶ፣ እንደአንድ ሰው እንዲነሳ ለማድረግ፣ ይህም ህዝብ ሶስቱን ጠላቶች በማያዳግም አኳኋን እንዲደመስሳቸው ለማድረግ፣ ገና ብዙ የትግል ጎዳና ይቀረናል። ስለሆነም፣ ሰፊው ህዝብ ለአብዮቱና ላገሩ አንድነት ለመሰዋት በተዘጋጀበት ባሁኑ ወቅት፣ ደጋግመን ለማሳሰብ የምንፈልገው፣ እየተዋጋና እየተከላከለም፣ ካሁኑ ለረጅም ጊዜ ትግሉም እንዲዘጋጅ ነው።

በሚዘጋጀው ዘመቻ ለኢትዮጵያ አብዮት ከፍተኛ ድሎችን ለማስገኘትና አብዮቱን ከቅልበሳ ለማዳን የሚያስችለው አማራጭ የሌለው ብቸኛ ጎዳና አብዮቱን ማፋፋም ብቻ እንደመሆኑ መጠን፣ አብዮቱን ማፋፋምም ለረጅም ጊዜ ትግል እንደመዘጋጀት ይቆጠራል። የኢትዮጵያ አብዮት በደረሰበት ደረጃና ባሉት ያገሪትዋ ችግሮች፣ ይህ አብዮት ዛሬ እንኳንስ ወደኋላ ሊያሽገሽግ ቀርቶ ባለበትም እንኳን ለመቆም ቢሞክር እንደሚደመሰስ እርግጠኞች መሆን አለብን። ስለዚህም ነው አብዮቱን መፋፋም አማራጭ የሌለው ጎዳና ነው የምንለው።

ግን ደግሞ አብዮቱን ማፋፋም ማለት ምን ማለት ነው?

አብዮቱን ማፋፋም ማለት፣ የተዘጋጀውና የሚዘጋጀው ዘመቻ ንፁህ ወታደራዊ ድርጊት ሳይሆን፣ ካገሪትዋ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና የማህበራዊ ኑሮ ጉዳዮች ሁሉ ጋር የተያያዘ መሆኑን ተገንዝቦ፣ በነዚህ መስኮች ሁሉ የሚካሄዱትን ትግሎች ከዘመቻው ጋር ማቀነባበር ማለት ነው። እንደዚሁም አሁን ባሉት ያገሪትዋ ችግሮች ላይ ሌሎች ሊጨመሩ እንደሚቻሉ አስቀድሞ ለማየትና ለነዚህም ችግሮች መዘጋጀት ማለት ነው። ለምሳሌ በጂቡቲ ነፃነት ሳቢያና በነሳኡዲ አረቢያ ድጋፍ አማካይነት፣ የአሊሚራህ ሰዎች በአፋር በኩል አዲስ ግንባርን ሊፈጥሩብን ይችላሉ። ኢምፔሪያሊዝምም በኬንያ በኩል እንደዚሁ ሊሞክር ይችላል። የቀዳሚ እለቱን ሰልፍ ያየው አድሃሪው ቢሮክራሲ ሴራዎቹንና ተንኮሎቹን የበለጠ ረቂቅ በማድረግ ለፀረአብዮት ሃይሎች መስራቱን ይቀጥላል፣ ወዘተ። ስለዚህም፣ ለአገሪትዋ አብዮትና ለአንድነትዋ የሚደረገው ተጋድሎ ዛሬ ካለው ሁኔታ አስር እጅ ወይንም መቶ እጅ የበለጠ የሰፊውን ህዝብ ተሳትፎ የሚጠይቅበት ጊዜ ይመጣል ማለት ነው።

በዚህ ሁኔታ፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ፣ የማህበራዊ ኑሮ፣ በዲፕሎማሲና በወታደራዊ መስኮች አገሪትዋ አቀነባብራ ልታካሂደቸው የሚገቡአት ትግሎች እጅግ የተወሳሰቡና አስቸጋሪ ስለሚሆኑ፣ ካሁኑ አንዳንድ እርምጃዎችን በመውሰድ፣ ለተባለው ረጅምና መራራ ትግል ዝግጅት ለማድረግ ይቻላል። ከነዚህም እርምጃዎች ውስጥ አንዳንድቹን ባጭሩ ለመጠቆም ያህል፣ በኢኮኖሚ በኩል የስራአውን ቁጥር አሁንም ይበልጥ ለመቀነስና አዳዲስ የስራ መስኮችን በተቻለ ፍጥነት ለመክፈት ጥረት ማድረግ፣ ዋጋን መቆጣጠር፣ ወዛደሩና አርሶአደሩ ምርትን ከፍ እንዲያደርጉ መቀስቀስ ያስፈልጋል። በፖለቲካ በኩል፣ የተራማጆችን ህብረት ማጠንከር፣ ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ለሰፊው ህዝበ ማወቅ፣ የብሄረሰቦችን መብቶች ካሁኑ ደረጃ በደረጃ ከስራ ላይ በማዋል የሰፊውን

ህዝብ ተሳትፎ እጅግ በጣም መጨመር ያስፈልጋል፡፡ እንደዚሁም፣ አብዮት የፈጠራቸውን አዳዲስ ህዝባዊ ድርጅቶች፣ ማለትም የገበሬ ማህበራትን፣ የቀበሌ ማህበራትንና ሌሎቹንም የህዝብ ድርጅቶች ማጠንከር፣ የነዚህን ህዝባዊ ሃይሎች የንቃትና የትጥቅ ሁኔታ በፍጥነት ከፍ ማድረግና ሰፊው ህዝብ የራሱን ነፃ እርምጃዎች የሚወስድበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ይህንንም ለማድረግ፣ ውስጥ ውስጡን ተደራጅቶ በተቀናበረ መንገድ በአብዮቱ ላይ የሚያሻጥረውን ቢሮክራሲ ያላንዳች ማወላወል መታገል ያስፈልጋል፡፡ በመጨረሻም፣ በማህበራዊ ኑሮና በወታደራዊ መስኮች፣ በዲፕሎማሲ፣ ባሁኑ ሰዓት መንግስት ሊወስዳቸው የሚችለውን እርምጃ ሁሉ ካለው ትግል አንፃር፣ የሰፊውን ህዝበ ሙሉ ድጋፍና ተሳትፎ ከሚያስገኝ መንገድ ሁሉ ከስራ ላይ ለማዋል መጣጣር፣ ለሚካሄደው ዘመቻ የማይበገር ደጀንን ለመፍጠር ይችላል ብለን እናምናለን፡፡ ለዚህም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ካድሬዎችን በህዝቡ ውስጥ ማሰማራት ያስፈልጋል፡፡

ዞሮ ዞሮ የነዚህ ጥያቄዎችና ዝግጅቶች ሁሉ ቁልፍ የሰፊው ህዝብ ይበልጥ መንቃት፣ መደራጀትና መታጠቅ፣ ማለትም በመሰረቱ የፖለቲካ ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ፣ ቅድሚያውን ለፖለቲካ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮታውያንና ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ከሁሉም በላይ እምነታቸውን መጣል ያለባቸው በሰፊው ህዝብ ላይ ነው፡፡ በሰፊው ህዝብ በሙሉ ልብ ለመተማመን እንደሚቻል ደግሞ ባለፈው ቅዳሜ የተሰለፉት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አርሶአደሮች በተጨባጭ መንገድ አሳይተዋል፡፡

የቅዳሜ፣ ሰኔ 18 ቀን፣ ወታደራዊ ሰልፍ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቦታን የሚይዝ ሰልፍ ነው፡፡ የዚያ ከፍተኛ የአርሶአደር ቁጥር በወታደራዊ ስልት መሰልጠንና መታጠቅ እራሱ ለክፉም ለደጉም በወደፊቱ የኢትዮጵያ አብዮት ሂደት ላይ ተጽእኖውን እንደሚያኖር ሳይታለም የተፈታ ነው፡፡ ይህንን ሰራዊት በትክክለኛው ጎዳናና በርግጥም በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ለመምራት ከተቻለ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ትላልቅና አስደናቂ ድሎችን ሊያገኝ ይችላል፡፡ በሌላ ደግሞ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ስህተቶች ከተፈፀሙና ይህንን ሰራዊት በሚገባ ለማሰለፍ ካልተቻለ የኢትዮጵያ አብዮት በጣም አስቸጋሪ ቀናት ሊያጋጥሙትና ሂደቱን ሊያዘጋዩት ይችላሉ፡፡ የፊተኛው ከደረሰ እጅግ በጣም ጥሩ ነው፡፡ የኋላኛው ከደረሰም የኢትዮጵያ ህዝቦች ከተጋድሎአቸውና ከልምዳቸው ተምረው ትግሉን ይቀጥሉና በመጨረሻም ያሸንፋሉ፡፡

አብዮቱን ለማዳን፣ አብዮቱን ማፋፋም
ዲሞክራሲያዊ መብቶች ለጭቁኖች ያለገደብ
የማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ህብረት ይጠንክር
የነቃ፣ የተደራጀና የታጠቀ የሰፊው ህዝብ ትግል ያሸንፋል

## አብዮቱ አጥቂነቱን እንዲቀጥል፣ ያድሃሪውን ቢሮክራሲ አሻጥር እንቋቋም

አድሃሪ ሃይሎች በኢትዮጵያ ከተሞች የሽብር ፈጠራ ዘመቻቸውን ከጀመሩበት ከመስከረም ወር 1969 ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ከቀበሌ ማህበራት ሊቃነመምብርት፣ ምክትል ሊቃነመናብርቶችና ከፀሃፊዎች፣ ከፍርድ ሸንጎ፣ የአብዮት ጥበቃና የህዝብ ደህንነት አባሎች ውስጥ 62 ጓዶች ከአድሃሪዎቹ ጥይት ወድቀዋል፣ 93 ጓዶች ተስለዋል።።

ደጋግመን እንደገለጽነው አብዮት መራራና ብዙ መስዋእትነት የሚጠይቅ ተጋድሎ ነው።። ታጋዮች ከጎናችን እየተቀነጠሱ ቢወስዱብን የነሱን የትግሌ አርማ አንስተን እኛ መቀጠል እንዳለብን እናውቃለን።። በነዚህ በተሰውት ጓዶች ምክንያት በየጊዜው የትግል ቃልኪዳናችንን እያደስን በንፁህ ደማቸው የተነከረውን የትግል አርማ እያነሰን፣ ታጋይ ይሞታል እንጂ ትግል አይሞትም እያልን እስካሁን ወደፊት በመጓዝ ላይ ነን።። እስካሁን አድሃሪዎች እንደተመኙት መሪዎቻቸው በነጭ ሽብር ስለተመቱ የቀበሌ ማህበራት አልፈረሱም፡ ፡ ሰፊው ህዝብ ተሸብሮ ወደዚያ የባርነት ስርዓት ተመልሶ መግባትን አልመረጠም።።

ነገር ግን ደጋግመን እንደገለጽነው በጓዶች መስዋእትነት ትግሉ ወደፊት ሊቀጣጠል የሚችለው ከነዚህ ጓዶች ሞት አስፈላጊውን ትምህርት ስንቀስም ብቻ ነው።። ሰኔ 14 ቀን 1969 የአብዮቱን የመጨረሻ መስዋእትነት ተቀብሎ ህይወቱን ለውድ እናት እገሩ አሳልፎ በሰጠው በጓድ አምበርብር በላይ የቀብር ስነስርአት ላይ የተሰበሰበው ህዝብ ደጋግሞ ያስተጋባው መፈክር አብዮታችን ከአጥቂነት ወደተከላካይነት ማፈገፈስጉ አንገብግቦናል የሚል እንደነበረ ይታወሳል።። በኛ ግምት ታጋይ ጓዶችንና አብዮታችንን በማስጠቃት ላይ ያለው አንዱና ዋነኛው ምክንያት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አድሃሪው ቢሮክራሲ በቀበሌ ማህበራት ተመራጮች ላይና በጠቅላላው በተራማጆች ላይ የሚያደርገው ተጽእኖ ነው።። የቀበሌ ተመራጮችን በማሰር፣ በማንገላታት፣ ነፃ ርምጃ እንዳይወሰዱ ያፍናል።። የታወቀ አድሃሪዎችን ጠቁመው አስይዘው ዘወር ከማለታቸው ቢሮክራሲው የተረከባቸውን አድሃሪዎች እንኳን ተገቢ ቅጣት ሊሰጣቸው ይቅርና መልሶ ይለቅባቸዋል።። እነዚህም አድሃሪዎች በቀበሌያቸው ተመልሰው በመደንፋት የቀበሌ ተመራጮችንም ሆነ ህዝቡን ተስፋ ሊያስቆርጡ ይሞክራሉ።። አንዳንድቹ እንዲያውም በተለይ ቀበሌው ያልታጠቀ ከሆነ ይፋ የሆነ የማጥቃት ርምጃ ይወስዳሉ።። ባጭሩ የአብዮቱ ደጋፊዎች እንኳን ራሳቸው ነፃ ርምጃ እየወሰዱ የአብዮቱን አጥቂነት ሊያፋፋሙ ይቅርና በዛሬው ወቅት ህጋዊ በሆነ መንገድ እንኳን በአድሃሪዎች ላይ ርምጃ ለማስወሰድ ተስኖአቸው እናያለን።። ይህ እንግዲህ አድሃሪ ሃይሎችን እርበድብደን ይዘን ከነበረበት ከየካቲትና ከመጋቢት ወር ምን ያህል እንዳሸገሸገን የሚያሳይ ነው።። አብዮታውያንና ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት በአድሃሪው ቢሮክራሲ ረቂቅ ሴራ ባስቸኳይ ነቅተው የማያዳግም ርምጃ ካልወሰዱ ይህ አደገኛ ማሸግሽግ አብዮቱን ሊያጠፋ ይችላል።።

አብዮታችን በገቢር ወደአጥቂነት ካልተሸጋገረ፣ በዚህ መልክ የቀበሌ ጓዶች ብቻ ሳይሆኑ ተራማጆች ከያሉበት እየተለቀሙ መመታታቸው

ይቀጥላል፡፡ እንደኢትዮጵያ ባለች ግንባር ቀደም ድርጅት በሌለባት አገር የታጋይ ግለሰቦች ሞት ለአብዮቱ ወሳኝ የሆነ ሚና እንደሚኖረው ግልጽ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ ጓዶች ሲገደሉ፣ ከነሱ ሞት አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመን አብዮቱን ለማራመድ ተጨባጭ ርምጃዎች ካልወሰድን ታጋይ ቢሞት ትግል አይሞትም የሚለው አነገጋር ትርጉም የለሽ ይሆናል፡፡ የጓዶችን የትግል አርማ ይዞ ትግሉን መቀጠል ማለት ከነሱ ሞት ትምህርት ቀድሞ ወደፊት መገፋት ማለት ነው፡፡ በአሁኑ ወቅተ፣ ለብዙ ጊዜ ተተኪ የማናገኝላቸው ታጋይ ጓዶችን እያጣን ነው፡፡ እነዚህን ጓዶች ለማጣት የቻልንበት ዋነኛው ምክንያት አብዮታችን ወደ ተከላካይነት እያፈገፈገ በመምጣቱ ነው፡፡ የአድሃሪውን ቢሮክራሲ ሴራ አክሽፈን አብዮታችንን ወደአጥቂነት ካላሸጋገርነው በየእለቱ ከሚቀነጠቡት ጓዶቻችን ጋር አብዮታችንም አብሮ መገዝገዙን ይቀጥላል፡፡ ይህ ደግሞ ቅልበሳን መጋበዝ ነው፡፡

ጓዶች፡- ጋዜጣችንንና የሌሎች ድርጅቶችንም ጋዜጦች አንብቡ፣ አስነብቡ፣ ተወያዩቱባቸው፣ ይዞታቸውን በሚገባ መርምሩ፡፡ አብዮታዊ ሂሶቻችሁን ሰንዝሩ፡፡